የሰ/መ/ቁ. 59537

ሚያዝያ 19 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** አነዚር ኢብራሂም - አልቀረቡም

**ተጠሪ፡-** የቤ/ጉ/ክ/ሥ/ፀ/ሙስና ኮሚሽን ዐ/ሕግ አቶ አብዮት አልቦሮ ቀረቡ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ሲሆን መርምረን የሚከተለውን ትዕዛዝ ሰጥተናል፡፡

## ት ዕ ዛ ዝ

አመልካች በሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ተከሳሽ ሲሆን ተጠሪው ደግሞ ከሳሽ ነበር፡፡ የሥር ከሳሽም በአመልካች (በሥር ተከሳሽ) ሁለት ክሶችን አቅርቧል፡፡ 1ኛ ክስ ተከሳሹ ቀደም ሲል በክልሉ የሥራ አመራር ተቋም ሀላፊ የነበረ ሲሆን ከዚሁ ከተጠቀሰው ተቋም ወደ ክልሉ አቅም ግንባታ ቢሮ ከተዛወረ በኋላ የሥራ አመራር ተቋም በጀት በሆነው በስልክ መስመር ቁጥር 0911254789 በህገ ወጥ መንገድ ተጠቅሞ ብር 4,674.32 የመንግሥት ገንዘብ ወጪ ሆኖ እንዲባክን በማድረጉ በሥልጣን ያለአግባብ በመገልገል በወ/ህ/ቁ 407/1ሐ/ የተመለከተውን ተላልፏል የሚል ሲሆን፤ 2ኛ ክስ ደግሞ ተከሳሹ በሥራ አመራር ተቋም ሥራ አስኪያጅ ሆኖ በሚሠራበት ወቅት በሥራ አጋጣሚ በትውስት በእጁ የገቡትን የመንግስት ንብረቶች እንዲመልስ በተደጋጋሚ ተጠይቆ ጠፍተውብኛል በማለት ያለአግባብ በንብረቶቹ ለመጠቀም አስቦ የሰወራቸው በመሆኑ በወ/ህ/ቁ/አ 413 (1ለ) የተደነገገውን የመሰወርና የወውሠድ ወንጀል ፈጽሟል የሚል ነው፡፡

ተከሳሹም ፍ/ቤት ቀርቦ የእምነት ክህደት ቃሉን ሲጠየቅ ወንጀሉን አለመፈፀሙንና ጥፋተኛ አለመሆኑን ክዶ በመከራከሩ የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት የከሳሽ ማስረጃዎችን ከሰማ በኋላ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 141 መሠረት ተከሳሹን በብይን በነፃ አሰናብቷል፡፡

በተከሣሹ በነፃ መለቀቅ ቅር የተሰኘው የሥር ከሳሽም ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን የጠቅላይ ፍ/ቤቱ ይግባኝ ሰሚው ችሎት በወ/ይ/መ/ቁ 01966 በቀን 24/02/2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት በአብላጫ ድምፅ በሰጠው ትዕዛዝ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 195(1) መሠረት የይግባኝ ባዩን ይግባኝ ባለመቀበል አሠናብቷል፡፡ ይሁን እንጂ አነስተኛው ድምፅ መልስ ሰጪው በሥር ፍ/ቤት ሳይከላከል በነፃ መሠናበቱ ያለአግባብ በመሆኑ መከላከል አለበት ብሏል፡፡

የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የወንጀል ይግባኝ ሰሚው ችሎት በአብላጫ ድምጽ የከፍተኛውን ፍ/ቤት ብይን በማጽናቱ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት የአሁኑ ተጠሪ ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታውን ያቀረበ ሲሆን ችሎቱም በመ/ቁ 02083 በቀን 19/11/2002 ዓ.ም

በዋለው ችሎት በአብላጫ ድምፅ በሰጠው ፍርድ ከሳሽ (ይግባኝ ባይ) በሁለቱም ክሶች አስረድቶ እያለ አልተመሠከረበትም በሚል በነፃ መለቀቁ ያለአግባብ ነው በማለት በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 142(1) መሠረት እንዲከላከል ወስኗል፡፡ የሰበር ችሎት አነስተኛው ድምጽ ደግሞ ተጠሪው (የሥር ተከሳሽ) ሊከላከል አይገባም ብሏል፡፡

በክልሉ ሰበር ሰሚው ችሎት ፍርድ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል ያለው የአሁን አመልካችም ሐምሌ 30 ቀን 2002 ዓ.ም በተጻፈ ቅሬታ በቀረቡብኝ ሁለት ክሶች የተጠሪ ምስክሮች የወንጀሉን ድርጊት አለመፈፀሜን በሚገባ በማረጋገጥ መስክረው እያሉ የክልሉ ሰበር ሰሚው ችሎት በአብላጫ ድምጽ በሰጠው ፍርድ እንዲከላከል መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ስህተቱ ታርሞ የአብላጫው ድምጽ ፍርድ ተሽሮና አነስተኛው ድምጽ መካላከል የለበትም ያለው ፀንቶልኝ በነፃ እንድሰናበት ይወሰንልኝ ብሏል፡፡

ለዚህ የሰበር ቅሬታ ተጠሪው በቁጥር 01/2003 በቀን 02/05/2003 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካች ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት የለውም፡፡ ምክንያቱም አንድ ተከሳሽ ወይም ይግባኝ ባይ ወይም የሰበር አቤቱታ አቅራቢ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 184(መ) እና 195 መሠረት የጥፋተኛነት ወይም የቅጣት ውሣኔ ባልተሰጠበት ይግባኝም ሆነ የሰበር አቤቱታ ማቅረብ አይችልም፡፡ አመልካች የሚያነሣቸው ነጥቦች በመከላከያ ማስረጃዎች የሚረጋገጡ እንጂ በሰበር አቤቱታው ባቀረበው ሁኔታ የሚታመንበትና ተቀባይነት የሚያገኝበት አይደለም፡፡ በሁለቱም ክሶች ተጠሪ ባቀረባቸው የሰውና የጽሁፍ ማስረጃዎች ከተገቢው ጥርጣሬ በላይ የተመሠከረበት በመሆኑ የሥር ሰበር ሰሚው ችሎት በአብላጫ ድምጽ የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያልተፈፀመበት ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

አመልካች ተጠሪው ለሰበር ችሎት ለሰጠው መልስ የመልስ መልስ በማቅረብ ክርክሩን አጠናክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር ከዚህ በላይ እንደተጠቀሰው የቀረበ ሲሆን እኛም ይህ ሰበር ችሎት ጉዳዩን የመመርመር ሥልጣን አለው ወይስ የለውም የሚለውን ጭብጥ ይዘን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10(2) ሆነ በኢ/ፌ/ዲ/ሪ/ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3) ሀ መሠረት የፌ/ጠ/ፍ/ቤት መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበትን ማንኛውንም የመጨረሻ ውሳኔ ለማረም በሰበር ችሎት የማየት ሥልጣን ያለው መሆኑ የተገለፀ ሲሆን በዚህ በተያዘው ጉዳይ ግን በሥር የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት አመልካች የቀረቡበትን ክሶች ይከላከል መባሉ በጉዳዩ የመጨረሻ ውሳኔ ተሰጥቶበታል የሚያሰኝ አይደለም፡፡

ስለሆነም የሰበር አቤቱታው ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ለመቅረብ ብቁ ባለመሆኑ ውድቅ አድርገን መዝገቡን ዘግተን ወደ መዝገብ ቤት ተመላሽ እንዲሆን ብለናል፡፡

***የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡***

*ራ/ታ*